# ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) የአማራ ክልል ህዝቦችን በትክክል ይወክላልን?

ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ 09-29-17

ማንም ሰው በቀላሉ ሊገነዘበው እንደሚችለው የአንድ ድርጅት ስያሜም ሆነ ተግበራዊ እንቅስቃሴ በመጀመሪያ እወክለዋለሁ የሚለውን የህብረተሰብ ክፍል መምሰል ይኖርበታል፣ ለዚህም ነው የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ የሲቪክ ማህበራት በዋነኛነት ይዘውት የተነሱትን አላማና እንወክለዋለን የሚሉትን የህብረተሰብ ክፍል ማንነት በትክክል ሊያሳይ የሚችልና ይህንንም ሁኔታ በማያሻማ አኳኋን በሚገልጽ ስያሜ ጥላ ስር ተሰባስበው ለመደራጀትና አላማቸውንም ከግብ ለማድረስ ጥረት የሚያደርጉት።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)፣ መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ የኦሮሞ ህዝብ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ)፣ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበራት ኮን ፌዴሬሽን (ኢሰማኮ)፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ አሶስየሽን እና የኢትዮጵያ ህግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር በሚል ስያሜ ተደራጅተው የሚገኙት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክና የሞያ ማህበራት በግንባር ቀደምነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

ከላይ በምሳሌነት ያነሳናቸው ኢትዮጵያዊያን ፓርቲዎች፣ ሲቪክም ሆኑ የሞያ ማህበራት ለምን እንደተቋቋሙና የትኛውን የህብረተሰብ ክፍል እንደሚወክሉም ሆነ ምን አይነት ርዕዮተ-ዓለም ይዘው እንደተነሱ የመመስረቻ ጽሁፋቸውንም ሆነ ሌሎች ሰነዶችን በዝርዝር መመልከት አሊያም ማገላበጥ ሳያስፈልገን ስያሜያቸው ከሚያስተላልፈው ጥቅል መልዕክት በመነሳት ብቻ በቀላሉ መረዳት እንችላለን። ሆኖም ወደ ወቅታዊው የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ስያሜና አደረጃጀት ስንመጣ አንድም ተግባሩና የአባላት ስብጥሩ ከስያሜው ጋር የሚሄድ ሆኖ አናገኘውም፣ ሁለትም ቢያንስ የሚመራው ብሔራዊ ክልል ህገ-መንግስትን መሰረታዊ መርህ እንኳ የተከተለ አይደለም።

ምክንያቱም በብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ውስጥ ከአማራ ብሔር ተወላጆች በተጨማሪ ቢያንስ አገዎች (የጎጃምና የወሎ)፣ ኦሮሞዎች፣ ቅማንቶችና አርጎባዎች በአባልነት ብቻ ሳይሆን በማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ተመርጠው በንቃት ሲሳተፉና አመራርም ሲሰጡ ይስተዋላልና ነው። በእርግጥ እዚህ ላይ ከመጀመሪያውም ቢሆን ስያሜው ለምን ከኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) ወደ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄነት (ብአዴን) ተቀየረ የሚል ጥያቄ በማንሳት ከ23 አመት በኋላ ሳይቀር የሚከራከሩ አባላትና ደጋፊዎች መኖራቸው ይታወቃል።

ይህም ሆኖ እነዚህ ወገኖች ቀደም ሲል የነበረው የድርጅቱ ህብረ-ብሔራዊ ስያሜ መቀየር የግድ የሚል ሆኖ ከተገኘም የክልሉን ተጨባጭ ብሔር-ብሔረሰባዊ ስብጥር ያገናዘበ መሆን እንደነበረበት በማስረጃ አስደግፈው አጥብቀው ሲሞግቱ ይስተዋላሉ፣ ምክንያቱም ክልሉ በርካታ ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦችን አቅፎ ከመያዙም በላይ የክልሉ ህገ-መንግስት ከመግቢያው ጀምሮ በሚገኙት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በተለይም በአንቀጽ ስምንትና በአንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ ድንጋጌዎቹ ላይ በማያሻማ አኳኋን እንደተመለከተው የአማራ ክልል ህዝቦች እያለ በተደጋጋሚ ከመግለጹም በላይ የልኣላዊ ስልጣን ባለቤትነትንም ሆነ ከፌዴራሉ ህገ-መንግስት በሚጻረር አኳኋኗን በቅድመ ሁኔታ የታጠረ ቢሆንም የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች በሚያረጋግጥ መልኩ ነው የተቃኘው።

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች ስብጥር ሲታይም ቢያንስ የሚከተለውን ይመስላል፡

| ተ.ቁ | ብሔር/ብሔረሰብ | የህዝብ ብዛት | ሽፋን በመቶኛ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አማራ | 15,752,992 | 91.48 | በ1999 ዓ.ም የተካሄደ ቆጠራ ውጤት |
| 2 | አገው-አዊ | 595,878 | 3.46 | በ1999 ዓ.ም የተካሄደ ቆጠራ ውጤት |
| 3 | ኦሮሞ | 451,362 | 2.62 | በ1999 ዓ.ም የተካሄደ ቆጠራ ውጤት |
| 4 | አገው-ኽምራ | 238,653 | 1.39 | በ1999 ዓ.ም የተካሄደ ቆጠራ ውጤት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 5 | ቅማንት | 172,327 | 1.20 | በ1987 ዓ.ም የተካሄደ ቆጠራ ውጤት |
| 6 | አርጎባ | 70,012 | 0.41 | በ1999 ዓ.ም የተካሄደ ቆጠራ ውጤት |
| 7 | ጉሙዝ | 13,105 | 0.10 | በ1999 ዓ.ም የተካሄደ ቆጠራ ውጤት |

**ምንጭ፣ በዋነኛነት በታህሳስ 2000 ዓ.ም ታትሞ የወጣው የ1999 ዓ.ም የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ሪፖርት**

ይኸው በአንድ ብሔር ስያሜ የመዋጥ አስተሳሰብ የበላይነት የአማራው ብሔር ፖለቲከኞች ችግር ብቻ ሳይሆን የሌሎቹ ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦችና ፖለቲከኞቻቸውም ጭምር መሆኑን በርካታ ምሳሌዎችን በማንሳት ማሳየት ይቻላል። ሌላው ቀርቶ የክልሉን ህገ-መንግስት መሰረታዊ መልዕክትና የክልሉን ህዝቦች ወቅታዊ ሁኔታ በትክክል ማንጸባረቅ የነበረበት የክልሉ የህዝብ መዝሙር ስለ አማራ ክልል ህዝቦች የጋራ ክብር ሳይሆን ስለ አማራ ብሔር ህዝብ ክብር በሚሰብክ መልኩ ነው የተቃኘው ማለት ይቻላል። ለምሳሌ ከክልሉ ህዝብ መዝሙር ውስጥ የሚከተለውን የግጥም ስንኝ እንመልከት፥

…….

የአማራነት ክብር ደማቅ አርማ ይዘን፣

ከሌሎች ህዝቦች ጋር እኩል ተከባብረን፣

በፍቅር በአንድነት አብረን እንዘልቃለን።

ይህም ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች እነሱን በቀጥታ ሊወክል የማይችለውን የህዝብ መዝሙር እንደራሳቸው ቆጥረው እንዲዘምሩ ይጠበቃል። ለዚህም ነው ይህንን እውነታ በጊዜ የተገነዘቡት የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ተማሪዎች የክልሉን ህዝብ መዝሙር በሚዘምሩበት ወቅት ከላይ ከተጠቀሰው የግጥም ስንኝ ላይ ሲደርሱ እንዴ ይሄ ምን ማለት ነው? እኛ ኦሮሞዎች ሆነን ሳለን በምን ምክንያት ነው ለአማራ ህዝብ ክብር ብቻ የምንዘምረው? የሚል ምክንያታዊ የሆነ ጥያቄ በማንሳት የብሔረሰብ አስተዳደር አመራሩን ሲያፋጥጡት አይ መልዕክቱ እንደዛ የሚል ከሆነማ የክልሉን የህዝብ መዝሙር ትታችሁ የኢትዮጵያን ህዝብ መዝሙር ብቻ ዘምሩ ሲል ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት የተገደደው። እርግጠኛ ነኝ ይህንን ሀቅ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሀላፊዎችን ጨምሮ የክልሉ መንግስት ባለስልጣናትም ሆኑ የብአዴን መሪዎች በትክክል የሚያውቁት አይመስለኝም። ይህንን ያልሁበት ምክንያት ከሶስትና አራት አመታት በፊት ለጥናት ወደ ባህር ዳር ሄጄ የክልሉን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉበኤና የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን በቃለ መጠይቅ መልክ እያነጋገርኳቸው በነበረበት ወቅት ለመሆኑ የኦሮሞ ብሔረሰብ ተማሪዎች የክልሉን የህዝብ መዝሙር እንደማይዘምሩ ታውቁ ይሆን? የሚል ጥያቄ ሳነሳላቸው፣ እረ በፍጹም ከማለት አልፈው እንዴት ተደርጎ ነው የክልሉ የህዝብ መዝሙር ሳይዘመር የሚቀረው? ይኸማ የክልሉን ህግ እንደ መጣስ ይቆጠራል? በማለት በሁኔታው በመደነቅና በመገረም መልኩ ከመመለስ አልፈው የችግሩን ምንጭ ከመረዳት ይልቅ ለምን የክልሉ ህዝብ መዝሙር አልተዘመረም ወደሚል ቁጭት የገቡት።

ሌላም ተጨባጭ ምሳሌ አንስቼ ለማሳየት ልሞክር፣ ከላይ በጠቀስሁት የስራ አጋጣሚ በክልሉ ውስጥ የሚገኙት አናሳ ብሔረሰቦች መብት በክልሉ ህገ-መንግስትም ሆነ በተግባር እየተከበረ ነው ወይ የሚል ጥያቄ አንስቼ በምንወያይበት ወቅት ከመልስ ሰጭዎቹ የተነሳው ችግር የብሔረሰቦቹ አስተዳደሮች ከሌሎቹ የዞን አስተዳደሮች ያን ያህል ተለይተው እንደማይታዩ ይልቁንም በበጀት ምደባና ዳኞችን በመሾም እንዲሁም ህግ በማውጣት ረገድ ወሳኝ የሆነ ስልጣን እንደሌላቸው ነበር ያረጋገጠው።

በዚህ አጋጣሚ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆኑ የብሔረሰብ ተወካዮችን በአካል አግኝቼ ለመሆኑ ብአዴን የሚለው ስያሜ እናንተን በትክክል ይወክላችኋልን? የሚል ጥያቄ ሳነሳባቸው በድንጋጤ መልክ እየተመለከቱኝ ደግሞ ብለህ ብለህ ምን አይነት ጥያቄ ይዘህብን መጣህ? በል ተው ይህን ጉዳይ ሌላ ጊዜ በግል እንጫወተዋለን በማለት ነበር የመለሱልኝ። የሚገርመው ነገር ይህን በግርምት መልክ የተመለከቱትን ጥያቄ ቀደም ሲል ራሳቸው አንስተው በተለይም ባህር ዳር ከተማ ውስጥ የተገነባው የሰማዕታት ሀውልት የአማራ ክልል ህዝቦች መታሰቢያ እንዲባል ያደረጉት እነዚሁ የብሔረሰብ ተወካዮ ሆነው ሳለ የድርጅቱ ስያሜ አንድምታ ላይ ዝምታን መምረጣቸው ነው።

እንግዲህ እነዚህና መሰል ጉዳዮችን አንስተን ስንመለከት ብአዴን የአማራውን ብሔረር ህዝብ ጭምር አይወክልም የሚለውን ጽንፈኛ ክርክር ወደ ጎን ብንተወው እንኳ በተግባር ግን በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ብሔረሰቦች በተሟላ መልኩ የሚወክል ሆኖ አለመገኘቱ ብቻ ሳይሆን ይኸው የተሳሳተ ግንዛቤና ከአማራ ብሔር ውጭ ያሉትን ብሔረሰቦች ዘላቂ ጥቅምና ፍላጎት እንዲሁም ስሜት በአንዱ ወይም በሌላኛው ሁኔታ እየሸራረፈ የሚገኝ መሆኑን ከላይ ያነሳናቸውን ምሳሌዎች በአስረጅነት ማቅረብ ይቻላል። ይህም ማለት ከአምስት ሚሊዮን የሚበልጥ የአማራ ህዝብ ከክልሉ ውጭ እንደሚኖር እየታወቀና በዚህ ህዝዝብ ላይ የመፈናቀልና የመደብደብና የመዘረፍ ድርጊት ሲፈጸምበት ዝም ብሎ የሚመለከት ድርጅት በየትኛው ሞራሉ ነው እወክለዋለሁ የሚለው?

በመሆኑም ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) በእርግጥም የአማራ ክልል ህዝቦችን በትክክል እንዲወክልና ማንነታቸውም ጎልቶ እንዲታይ ካስፈለገ ቢያንስ በክልሉ ህገ-መንግስት እውቅና ያገኘውን የሁሉንም የአማራ ክልል ህዝቦች አቃፊነት መንፈስ በመሪ ድርጅቱ ስያሜም ጭምር ጎልቶ መታየት ስላለበት በዚህ አመት አጋማሽ ላይ እንደሚካሄድ በሚጠበቀው ድርጅታዊ ጉባኤው ላይ ይህን ሀሳብ በአጀንዳነት ይዞ ከመወያየት አልፎ ስያሜውንም በማስተካከል በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች በሚወክል መልኩ መቃኘት ይኖርበታል የሚል እምነት አለኝ፣ ከዚህ አንጻር በአማራጭነት ሊቀርቡ ከሚችሉ ስያሜዎች መካከል የአማራ ክልል ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ድርጅት (አክህዴን/ድ) አንዱ ሊሆን ይችላል ብየ አምናለሁ።